# ትዝታ

ልሂድ ልብረር ልውጣ ይውሰደኝ ንፋሱ
አሞራን ልከተል አልለይም ከሱ::
ደመናውን ልልበስ ልሸፈን ይብረደኝ
ውሀ ሆኖ ጠፍቶ ፀሐይ እስኪፈጀኝ::
ልንሳፈፍ ባየር ላይ ልመልከት መስኮችን
በያይነቱ አበባዎች ቀያይ ቢጫዎቹን::
ወንዞችን ልያቸው እጥፍ ዘርጋ ሲሉ
ተራራውን ሰንጥቀው ሲያልፉ በማህሉ
እግሬ አፈሩን ይርገጥ ልምጣ መሬት ልንካ
ዛፍ እንጨቱን ልየው እልም ባለ ጫካ
እንቅፋትም ይምታኝ እሾክ ይውጋው እግሬን
ከእንቅልፌ እንድነቃ እንዳውቀው መኖሬን::
ስወድቅ ልንከባለል ልብሴን አፈር ይንካው
ደጡ ላይ ልንሻተት ያበላሸኝ ጭቃው::
ልንቦራጨቅ ልግባ ጎርፉ ይውሰደኝ
እግሬን ላፈራርቀው ያለትን ብልሀት
ውሀስ ሰውነቴን ያርስ ያለስልሰው
ፏፏቴ ያጓራ ያንሳፈኝ አረፋው::
ተወርውሬ ልውጣ ባሸዋው ላይ ልሩጥ
የግሬን ምልክቶች ልተው መሬቱ ውስጥ
ትንፋሼ ይቆረጥ ፍጥነቴን ልቀጥል
ነፋስ ቡቃያውን ልየው ሲያመሳቅል
በተራ ሊያስተኛው አጥሮ ሲዘረጋው
ማዕበል አስመስሎ እየቆራረጠው
የታጨደው ክምር ፈርሶ ሲንገላታ
አየር ላይ ሲወጣ ባውሎ ነፋስ ዋልታ
ከውስጡም ልውደቅበት ፍራሽ ይሁን ሣሩ
መዓዛው ይሸተተኝ የሚጣፍጥ ማሩ
ከዛፍ ጥላ ሥር ይለፍልኝ ቀኑ
እረኛው ሲዘምር ሲያሞግስ ከብቶቹን
ወዲያ ወዲያ ደግሞ ጋራው ጥላ ሲሆን
አረሁ ሲደበቅ ሜዳው ሲዥጎረጎር
ዛፍ እየጠቆረ ከሩቅ ያለው መንደር
በጥስ ተሸፍኖ መልኩን እያሰላ
ውበት ማታ መጣች የቀኑን ጨርሳ::
ፀሐይ የሞቀውን ተጎናፅፋ ልብሷን
ቀስ ባለ ብጫ ሸፍናው ፍጥረትን::
ስትሄድ ስታሾልቅ ስትዘቀዘቅ
እነሆ ጌጦቿ አለማዝና ወርቅ
መሬት ሲዘቀዝቅ ሲፈካ ቀላዩ
ጨረቃና ኮከብ አንድ ላይ ሲታይ
ፊቴን ስዳበሰው ቀዝቃዛ ሽውታ
ሰውነቴን ትቼ እስቲ ልረፍ ማታ::

---

# ስንኖር

ሁሉም ይለወጣል
ያለፈው ጨልሟል
ግልፅ ነው ዛሬ ቀን
አናውቅም መጪውን
አዲስ መንገድ አለ
ሰው ካዘነበለ
ወደስሜቱ ግብ ወደልቡ እርምጃ
ካየ ካስተዋለ ካሰበ ከሔደ
መጥፎ ነው ያለውን ለምዶት ከወደደ
የሚፈልገውን አያጣውም እንጃ
ምንድነው ብቻነት? እየኖሩ መጥፋት
ከሰው ማህል መውጣት
ከሀሳብ ጎዳና መብረር መባከን
ለመያዝ መሞከር የማያዩትን
በሀዘን ምን አለ? ደስታስ ምንድነው
ሰመመን ትካዜ ምን መሠረት አለው?
ሳቅ ጨዋታ ፍቅር ምንድነው አይነቱ
ጥላቻና ቁጣ ወዴት ይሆን ቤቱ?
ይህ ሁሉ ሃሳብ ነው
ሐሳብ ግብ ይኑረው
ሔዶ ዞሮ ዞሮ ይመለስ ከቦታው
ይታይ መልኩ ይውጣ ይውረድ ክንብንቡ
ይናገር ያስረዳ ይገለጥ ጥበቡ።

ሐሳብ ነው ሥራችን
ነው ሐሳብ ኑሯችን
አመል ጠብቆ ነው
ገላን የሚያለብሰው
የልጅነት አመል የልጅነት ልብስ
ሲያድጉ የሚቀር ነው የሚበጣጠስ
አዲስ ልብስ ይሰፋል
አዲስ እድገት ሞልቷል
ያልደረጀው ጊዜ ልጅ የሚኖርበት
ይሻራል ይቀራል ይረሳል ሲተዉት
የማኅበር ኑሮ
የድሮውን ሽሮ
በሰፊው ይገልፃል ብዙ ጓዝ ያመጣል
ማስተካከል ያሻል።

--------------------------------

፲፱፻፶፮

# የፍቅር ሰላምታ

ጠጉርሽን ዳብሶ በጆሮሽ ያለፈው
ነፋሱ ምን አለሽ?
በመስኮት ላይ ሆነሽ
የፍቅሬን ሰላምታ ስያስተጋቡ ይዘው
ተራሮች የላኩት
በሩቅ የሚታዩት
የሚወዛወዙት ቆመው በመስኮትሽ
ዛፎቹ ምን አሉ?
ይንሾካሾካሉ።
አይተዋል ደብዳቤ ማታ ስፅፍልሽ
ይግለፁ ምስጥሩን
ልቤ መሸበሩን።
ልብስሽን ስትለብሺ ወፎች የሚዘፍኑት
የሚሉት ምንድን ነው?
ጡቶችሽን አይተው
በፍቅርሽ ሰላምታ ልቤን እያደከሙት
ላኪያቸው ይምጡልኝ
መድኃኒቱን ይስጡኝ።
ኮኮቦች ከሰማይ ይጠቃቀሳሉ
ውበትሽን አይተው
በቅርፅሽ ተደንቀው።
በሰማዩ ባህር ጠልቀው ይዋኛሉ
ፍቅርሽን ሊይዙ
ወደኔ ሊጓዙ።
ምን አለች ጨረቃ በመስኮትሽ ገብታ
ስትነካ ፊትሽን
ተደግፋ አልጋሽን።
ልኬልሽ ነበረ የፍቅር ሰላምታ
ጠይቅያት ውሰጂ
መልሱንም ስደጂ።
የቤተክርስትያን ደወሉ ዘመረ
ምን ሆኖ ይጮኻል?
ሰው ይሰበስባል።
ጉዳችንን አይቶ ገልጦ ተናገረ
እባክሽ ለፍቅር ሞተን እንቀበር።
ምነው ምን ፈለገ ሲጨፍር ከበሮ?
ተነሳ የሚለኝ
የሚቀሰቅሰኝ።
ፍቅርሽን ፍቅሬን በመሐረም አስሮ
እንሒድ ተቃቅፈን
ደብቆ ይውሰደን
የበረረው ልቤ ካጠገቤ ጠፍቶ
ምን ምሥጢር አወራ?
ደንግጦ እየፈራ።
ስታንጎራጉሪ መኝታሽ ቤት ገብቶ
የፍቅሬን ሰላምታ
ይስጥሽ በቀስታ።

---------------------------------------

፲፱፻፶

## አስደንጋጭ

የፈነዳ አበባ .....
ሠይጣን የቀናባት
እንደ መልአክ ቆንጆ ነበር ውበቷ
ዘመናይ እመቤት።
አልማዝ ያስነጠፈች
ወርቅ ያስጎዘጎዘች
በሻነል በዲዮር ሽቱ የታጠበች።
በጌጥ አብረቅርቃ
ጌጥ ሆና ግጥ ይዛ።
ጨረቃ ታፍራለች
ፀሐይ ትጠፋለች
ፀዳል፣ ብርሀን ፣ ንጋት ሁሉን ታስንቃለች
ስትናገር ስቃ
ድምጿ ነው ሙዚቃ።
ማር እንጎቻ ከንፈር .....
ንግግሯ ሕይወት ፈገግታዋ ምሥጢር
አልባብ ጠረን አፏ ጨዋታዋ ፍቅር
ውብ የውብ ውብ ውብ ናት
የሌላ ዓለም ውበት
በከንፈሯ ገዳይ ጥርሷን አሳይታ
በጡቷ ተዋጊ ዳሌዋን መክታ
የሠራ አከላቷ ባለ ግርማ ሞገስ
ሰው የሚያፈራርስ።

-------------------------------

## አርእስት የሌለው

ሕይወት ጨለማ ነው የምንጓዝበት
ደስታችን መብራት
መንገድ አሳይቶን ወዲያው የሚጠፋ
የመከራ ዝናም ችግሩ ሲያካፋ።

-------------------------------

፲፱፻፶

## የባህር ቅርደዶች

የሚሽቀዳደሙት የባህር ቅርደዶች ወዳሸዋው
የፀሐዩን ጮራ ይዘው እየሮጡ።
ይርመሰመሳሉ ይረበረባሉ
ይብረቀረቃሉ
ምንድነው ጉዳዩ!
ነፍስ አስቆጥቶ የሚያሯሩጣቸው?
ተልከው ይሆናል አንድ ነገር ይዘው።
ከባህሩ ማህል አሳው ሲነጋገር
ወይም ከሩቅ ጠረፍ መርከብ ሲሽከረከር
ወይ ከጀልባው ስር።
ማዶ ከሚታየው ከትንሹ ደሴት
ከተንዘራፈጠው ከጋራው አቀበት።
ይዘዋል በመላ።
ማን ያውቃል ምን ይሆን?
ትርጉሙ ረቂቅ ነው የቋንቋቸው መጠን።
እነሱም አያውቁት (ይቻላል ለማለት)
ምን እንደለገሣቸው አጥመልምሎ ድንገት።
ምን እንደሚሠሩ የት እንደሚሄዱ
የፀሐዩን ጮራ ሲያመጡ ሲወስዱ።
አሸዋ ሲገፉ
ዓሣን ሲሸከሙ ሲጥሩ ሲለፉ።
ዛጎል አንከባለው ወደ ዳር ሲያወጡ
ሲጋጩ ሲሮጡ።
አንዱ ሌላ ሲሆን እያበጀ ቅርድድ
ያኛው በመከተል የሱን ቦታ ሲወስድ።
ኑሮአቸው ነው ውሽት።
ምሥጢራቸው ባዶ አልቦ ነው ቀለበት
ይህ ሁሉ ድካም ከቶ ምንድን ነው?
መሬት ለማቅናት ነው?
አገር ለመያዝ ነው?
ልፋታቸው ከንቱ!
ግን ትርጉም ይሰጣል
ይኸ ነው እውነቱ
ሁኔታው ሲለወጥ የቅርድድነቱ።
ተንደርድሮ መጥቶ ሲሔድ ወደዋሻው
መሬቱ ሲውጠው።
ወደተነሣበት ዳግም ላይመለስ
ፈርሶ ሲበታተን ከጠረፉ ሲደርስ።
ቅርድዱ የታለ?
የድሮ ሁኔታ መልኩ ከተጣለ።
ያ ሁሉ መርመስመስ ያ ሁሉ ማብረቅረቅ
ያ ሁሉ መሯሯጥ ያ ሁሉ መፍለቅለቅ
ጠፍቶ ሲዘባረቅ።
መንቀሳቀሳቸው በኋላ ዝም ሲል
ከትንሽ አንስቶ ከቁንጫ ቅማል
ከዝሆን ከግመል።
በጣም አዋቂው እንስሳ ከሁሉ
ሰውን ይመስላሉ።

-------------------------------

፲፱፻፶፪

## እውር ቅናት ይዞኝ

እውር ቅናት ይዞኝ
ሴይጣናዊ ቁጣ
በቃን ይበቃና ብዬ ሆዴ ቆርጦ
አንቺ ስታለቅሺ ...
እቤቴ ገብቼ
ዓለም ባዶ ሆኖ
እምባዬን ጠርጌ ደግሞ አለቀስኩና
ፊቴን በመሃረብ ሸፍኜ ያዝኩና
እምባዬ ሲፈላ
ዓይኔን ሲያቃጥለኝ
ጉሮሮዬን አንቆኝ
ደቂቃው ሰዓቱ
ቆሞ ተንጠልጥሎ
ሃሳቤ ሲናወዝ
ይህ ነበር ትዝታሽ
ከእኔ ጋር የቀረው
መቼ ይሆን ጊዜው
ፍቅሬ የምረሳሽ
መቼ ነው? መቼ ነው?
እውር ቅናት ይዞኝ
ፀፀት አተረፍኩኝ፡፡

--------------------------------

## አርእስት የሌለው

ፍቅርሽን በፍቅሬ በፍቅርሽ ልቅመሰው
ፍቅርሽን መንፈሴ በፍቅርሽ ይዳብሰው
ፍቅርሽን በሀሳብ በፍቅሬ ልቅመሰው
ፍቅርሽን እንደማር ባፌ ላጣጥመው
ፍቅርሽና ፍቅሬን አላሳይም ለሰው
ፍቅርሽን ልቅመሰው መከራዬን ልርሳው
ፍቅርሽ ለእኔ ህይወት ለኔ ሰፊ ዓለም ነው፡፡
ፍቅርሽ የማይሻር ዘልዓለማዊ ነው፡፡
ፍቅርሽ የኔ ብቻ የማይጠገብ ነው፡፡
ፍቅርሽ መጠጊያዬ ፍቅርሽ ዓለሜ ነው፡፡
ፍቅርሽ ነው መሸሻ ፍቅርሽ ዋሻዬ ነው፡፡

----------------------------

## አርእስት የሌለው

እንደ መደውር ዘወትር ለምላሚቱ
በፍቅር አጠራር ልበልሽ ማሚቱ፡፡

1. ከንፈርሽ ብርቱካን አእምሮ ከሚመጥ
   የኔ ህይወት አንቺ ነሽ አልፈልግም መጠጥ
   ንግግርሽ ጣፋጭ አፍሽ ማር ወለላ
   ፈገግታሽ ምንድነው ህይወት የሚበላ፡፡

2. ሲጃራ አላጨስም ፍቅርሽ አስግቶኛል
   ትንፋሽሽ ጤና ነው በጣም ይሞቀኛል
   አተኩሮ ላየሽ መልክሽ ያስደንቃል
   ጥርስሽ ብቻ አይደለም አይንሽም ይስቃል፡፡

3. ጮራ ሲፈነጥቅ በማለዳ
   ጽጌሬዳ አብባ በፀሐይ ስትፈነዳ
   ማሚቱ ማምየ ማሚቱ ስልሽ
   እባክሽ ንገርኝ ምን ይላል ልብሽ፡፡

-------------------------------